## የአደጋ ጊዜ ግብዓቶች ዝርዝር

እርስዎን እና ቤተሰብዎን ቢያንስ **ለሶስት ቀናት** የሚያቆዩበትን በቂ ግብዓቶች ያዘጋጁ።



### የእርስዎ ኪት የሚከተሉት እቃዎች እንዳሉት ያረጋግጡ

- መድሃኒቶች
- ምግብ እና ውሃ
- የጨቅላ ህፃናት እና የልጆች ግብዓቶች
- የቤት እንስሳት ግብዓቶች
- ሞባይል ስልክ/ባትሪ መሙያ
- የእጅ ባትሪ እና ፋሽካ
- ጥሬ ገንዘብ
- የአስፈላጊ ሰነዶች ቅጂዎች
- የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ኪት
- በባትሪ የሚሰራ ራዲዮ እና ተጨማሪ ባትሪዎች

**የእራስዎን የዝግጁነት ኪት ይገንቡ፡-**

www.ready.gov/kit

## አስፈላጊ

### መድሃኒት የሚወስዱ ከሆነ

- ሁልጊዜ ቢያንስ ለአንድ ሳምንት የሚበቃ የመድኃኒት አቅርቦት ይኑርዎት።
- እርስዎ እና የቤተሰብዎ አባላት የሚወስዷቸውን መድሃኒቶች ይጻፉ።
- የመድኃኒቱን ስም፣ መጠኑን፣ በየምን ያህል ጊዜ እንደሚወስዱት እና ለምን እንደሚወስዱት ያካትቱ።

### መረጃን እያገኙ ለመቆየት እንደተገናኙ ይቆዩ

ነጻ የአደጋ ጊዜ ወይም የአየር ሁኔታ ማንቂያዎችን ከፊላደልፊያ ከተማ ያግኙ። ወደ **888-777 READYPHILA** ብለው መለዕክት ይላኩ ወይም ነጻ ማንቂያዎችን ለማግኘት ወደ **www.phila.gov/OEM** በመሄድ ይመዝገቡ።

### የማህበረሰብ ምላሽ አጋር አውታረ መረብ

ስለ ከባድ አውሎ ነፋሶች እና ሌሎች የህዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት ይቀላቀሉ።

ይመዝገቡ




https://bit.ly/CRPNnewsletters



# ከባድ የአየር ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ ጤንነትዎን እና ደህንነትዎን እየጠበቁ ይቆዩ

Department of Public Health
CITY OF PHILADELPHIA

# የአየር ንብረት ለውጥ ምን እያስከተለ ነው?

### ተጨማሪ ዝናብ

ከባድ እና ተደጋጋሚ አውሎ ነፋሶች ወንዞች፣ ሀይቆች እና ሌሎች የውሃ አካላት ብዙ ጊዜ እንዲጥለቀለቁ ያደርጋሉ።

### የአውሎ ነፋስ መባባስ

የባህር ዳርቻ አውሎ ነፋሶች እየጠነከሩ እና እየበዙ ነው እና ይህ ውሃ ከመደበኛ ወለሉ በላይ እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል።

### የባህር ወለል መጨመር

አንዳንድ የፊላዴልፊያ አካባቢዎች የባህር ከፍታ መጨመር እና የጎርፍ አደጋ ተጋርጦባቸዋል።



### ጄነሬተሮች እየተጠቀሙ ከሆነ

- ጄነሬተሮች መርዛማው ጋዝ ካርቦን ሞኖክሳይድን (CO) ያመነጫሉ።
- መስኮቶቹ እና በሮች ክፍት ቢሆኑም እንኳ ጄነሬተርን በቤት ውስጥ አይጠቀሙ። ከቤትዎ ውጪ ከ20 ጫማ ርቀት በላይ አስቀምጠው ይጠቀሙባቸው።

# በጎርፍ ጊዜ እና ከጎርፉ በኋላ ምን ማድረግ አለብኝ?

### ከጎርፍ ውሃ ራስዎን ይጠብቁ

- በጎርፍ በተሞሉ መንገዶች አይንዱ ወይም አይራመዱ።
- የጎርፍ ውሃ ጎጂ ጀርሞችን፣ ኬሚካሎችን እና ቆሻሻዎችን ይዟል።
- የጎርፍ ውሃ ከነኩ እጅዎን ይታጠቡ።

### ከወባ ትንኝ ንክሻዎች ራስዎን ይጠብቁ

- የተኛ ውሃ ያስወግዱ።
- የመስኮትና የበር መሸፈኛዎችዎ መኖራቸውን ያረጋግጡ።
- የወባ ትንኝ መከላከያ መድሃኒት ይጠቀሙ።

### የኤሌክትሪክ ኃይል ካጡ

- ከአራት ሰአታት በላይ በማይሰራ ማቀዝቀዣ ውስጥ የቆየ ምግብ ያስወግዱ።
- ማቀዝቀዣ የሚያስፈልጋቸውን መድሃኒቶች ይተኩ።

***የጎርፍ መጥለቅለቅ የጤና አደጋዎችን ጨምሮ በፊላደልፊያ ላሉ ሰዎች ብዙ አደጋዎችን ያመጣል።***

# ስለ ሻጋታ ምን ማድረግ አለብኝ?

### መከላከል

- ሻጋታን ለመከላከል እርጥበትን ይቆጣጠሩ።
- እርጥብ ቦታዎችን በ24 ሰአታት ውስጥ ያፅዱ እና ያድርቁ እና ሊደርቁ የማይችሉ ነገሮችን ያስወግዱ።
- ለማድረቅ የአየር ማራገቢያ፣ የአየር ማቀዝቀዣ እና የእርጥበት ማስወገጃዎችን ይጠቀሙ።

### ደህንነቱ የተጠበቀ ጽዳት

- የጎማ ጓንቶች፣ የአይን መከላከያ፣ ረጅም እጄታ ያለው ሸሚዝ፣ ረጅም ሱሪ እና ጨምብል ያድርጉ።
- በሮች እና መስኮቶችን ይክፈቱ።
- በአሞኒያ ያልተሰራ ደረቅ እና ፈሳሽ ሳሙና ይጠቀሙ። ማጽጃውን ከአሞኒያ ጋር በፍፁም አትቀላቅሉም።
- ከቻሉ ከ3 በ3 ጫማ በላይ የሆኑ ሻጋታዎችን ለማጽዳት ባለሙያ ይቅጠሩ።

**ሻጋታ የዓይን እና የቆዳ መቆጣትን እና የአለርጂዎች መነሳትን ሊያስከትል ይችላል።**

**አስም ካለብዎ፣ ሻጋታ አስምዎን ሊያስነሳብዎት ይችላል።**



ስለ ሻጋታ አጸዳድ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት
**www.epa.gov/mold**